# የገንዘብ ሚኒስቴር

## የታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ ለማድረግ የወጣ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 773/2013

የገንዘብሚኒስቴር

ሚያዝያ 2013ዓ.ም

# የታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ ለማድረግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 773/2013

## 1. አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ)አንቀጽ129(1) በተሰጠውሥልጣንመሠረትይህንንመመሪያአውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህመመሪያ "የታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ ለማድረግ የወጣ መመሪያቁጥር 773/2013ዓ.ም" ተብሎሊጠቀስይችላል፡፡

## 3. ትርጓሜ

ለዚህመመሪያ አፈፃፀም፡ -

1/ "ታክሲ" ማለት በከተሞች ወስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሾፌሩን ጨምሮ ከአራት እስከ 10 መቀመጫ ያለው ተሽከርካሪ ነው፡፡

2/ "ሙሉ በሙሉ የተበታተነ (Complete Knocked Down)"ማለትየንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚያወጣውን ማስፈርት በሚያሟላ ሁኔታ ወደአገር የሚገባ ተሽከርካሪ ነው፡፡

3/ "በከፊል የተበታተነ (Semi Knocked Down)"ማለትየንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚያወጣውን ማስፈርት በሚያሟላ ሁኔታ ወደአገር የሚገባ ተሽከርካሪ ነው፡፡

4/ "የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካ" ማለት ለታክሲ አገልግሎት የሚውልን ተሽከርካሪ አካላት ሙሉ በሙሉ በተበታተነ ወይም በከፊል በተበታተነ ሁኔታ ወደአገር በማስገባት ተሽከርካሪን የመገጣጠም ፈቃድ የተሰጠው ኢንዱስትሪ ነው፡፡

5/ "የታክሲ አገልግሎት ሰጪ ማህበር" ማለትየታክሲ አገልግሎት በሚሰጡ የተሽከርካሪ ባለቤቶች በአገሪቱ ሕግ መሠረት የተቋቋመና ከትራንስፖርት ባለሥልጣን ጋር በዚህ መመሪያ የተመለከተውን ውል የፈፀመ ማህበር ነው፡፡

6/ "ቀረጥና ታክስ" ማለት ወደአገር በሚገቡ ወይም በአገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ቀረጥና ታክስ ነው፡፡

7/ "ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን"ማለት በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 51 በተደነገገው መሠረት ፈቃድ በተሰጠው የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው ግብዓቶች የሚቀመጡበት መጋዘን ነው፡፡

8/ "ሚኒስቴር" ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማዎች፣

ሀ) ለማኅዋወጫ ለነዳጅ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪበማስከተል ላይ የሚገኙት በከተሞች አገልግሎት በማስጠት ላይ የሚገኙ ለበርካታ ዓመታት ያገለገሉ ታክሲዎች በአዲስ ተሽከርካሪ እንዲተኩ በማድረግ ሕብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኝ ማድረግ፣

ለ) በአወሮፕላን ማረፊያዎች፣ በሆቴሎች እና በሌሎችም የቱሪስት መዳረሻዎች በቂ የታክሲ አገልግሎት እንዲኖር በማድረግ ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ ማስፋፋት ምቹ ሁኔታን መፍጠር፣

ሐ) የአገር ውስጥ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካዎች ለተዘረዘሩት ተግባራት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን የሚያቀርቡበትን ሥርዓት በማዘርጋት ለኢንዱስትሪው ማስፋፋት እገዛ ማድረግ ናቸው፡፡

## 5. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ስለመሆን

በዚህመመሪያ የተቀመጡት ገደቦች እና ቅድመ - ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለታክሲ አገልግሎት ለሚውሉ ተሽከርካሪዎች ማምረቻ ሙሉ በሙሉ በተበታተነ ወይም በከፊል በተበታተነ ሁኔታ በተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካወደአገር የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ወደአገር በሚገቡ ወይም አገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ ከተጣለ ማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ተደርገዋል፡፡

## 6. የመብቱ ተጠቃሚዎች

1/ በዚህመመሪያ የተቋቋመው መብት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት የታክሲ አገልግሎት ሰጪ ማህበራት ብቻ ናቸው፡፡

2/ የታክሲ አገልግሎት ሰጪ ማህበራት በዚህ መመሪያ የተቋቋመው መብት ተጠቃሚ የሚሆኑት በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች የተገጣጠሙ ተሽከርካሪዎችን በሚገዙበት ጊዜ ይሆናል፡፡

## 7. የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካዎች ኃላፊነት

1/ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካዎች፡-

ሀ) ለታክሲ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን ለማምረት የሚውል የተሽከርካሪን ሙሉ በሙሉ በተበታተነ ወይም በከፊል በተበታተነ ሁኔታ ወደአገር በሚያስገቡበት ጊዜ፣

(i) በእነዚህ አካላት ላይ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ አስቀድመው ማከፈል፣ ወይም

(ii) የተሽከርካሪ አካላቱ የሚቀመጡበት ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ያላቸው ሆኖ፣ እነዚህን አካላት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በመጋዘኑ ማከማቸት፣ ይችላሉ፡፡

ለ) በተሽከርካሪዎቹ አካላት ላይ ቀረጥና ታክስ አስቀድመው የከፈሉ በመሆንበት ጊዜ ተሽከርካሪወን ገጣጥመው ለመበቱ ተጠቃሚዎች መሸጣቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባቀረቡ በ30 ቀን ጊዜ ወስጥ ለተሽከርካሪው ማምረቻ በዋለው ግብዓት ላይ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

ሐ) ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ወደቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን የገቡት የተሽከርካሪ አካላት ወደመጋዘን ከገቡበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ወስጥ ተሽከርካሪዎቹን በማምረት ለመበቱ ተጠቃሚዎች መሸጥ አለባቸው፡፡

መ) በዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል "ሐ" መሠረት የተመላሽ ጥያቄያቸወን ተሽከርካሪው በተሸጠ በ1 ዓመት ጊዜ ወስጥ ማቅረብ አለባቸው፡፡

2/ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካዎች በዚህ መመሪያ ለተመለከቱት የመበቱ ተጠቃሚዎች ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለመሸጥ የሚችሉት ከፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወል ለፈፀመ ማህበር በሚሸጥ የድጋፍ ደብዳቤ ብቻ ይሆናል፡፡

## 8. በሥራ ላይ ያሉ ታክሲዎችን በአዲስ ስለመተካት

በሥራ ላይ ያሉ ታክሲዎችን በአዲስ የሚተካ የታክሲ አገልግሎት ሰጪ ማህበር፣

ሀ) ሙሉ በሙሉ በተበታተነ ሁኔታ ወይም በከፊል በተበታተነ ሁኔታ ወደአገር በገቡ የተሽከርካሪ አካላት የተመረቱ አዲስ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ለመግዛት ይችላል፡፡

ለ) በአዲስ የሚተካቸው ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር የገቡ ወይም በአገር ወስጥ የተገዙ ከሆነ በሥራ ላይ ባሉ ተሽከርካሪዎች ላይ ቀረጥና ታክሱን የከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከጉምሩክ ኮሚሽን የተሰጠ ማስረጃ ለፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡ የጉምሩክ ኮሚሽን የዚህን ማስረጃ ቅጂ ለገንዘብ ሚኒስቴር ይልካል፡፡

## 9. አዲስ ተሽከርካሪን ስለመግዛት

የመበቱ ተጠቃሚ የሆነ የታክሲ አገልግሎት ሰጪ ማህበር በሥራ ላይ ያሉ ታክሲዎችን ለመተካት ሳይሆን አዲስ ተሽከርካሪ ገዝቶ በታክሲ አገልግሎት ሥራ ለማሠማራት በሚፈልግበት ጊዜ፣ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ለመግዛት የሚችለው ሙሉ በሙሉ በተበታተነ ሁኔታ ወደአገር በገቡ አካላት የተመረቱ ተሽከርካሪዎችን ብቻ ነው፡፡

## 10. የመበቱ አፈፃፀም

1/ የክልል መንግሥታት፣ የከተማ አስተዳደሮች እና የፌዴራልና የመንግሥት መ/ቤቶች ለታክሲ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ለመግዛት የሚፈልጉ የታክሲ አገልግሎት ሰጪ ማህበራትን ጥያቄ ከድጋፍ ደብዳቤ ጋር ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ይልካሉ፡፡

2/ የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን፡-

ሀ) ጥያቄው በሥራ ላይ ያሉ ታክሲዎችን በአዲስ ለመተካት ከሆነ የታክሲ አገልግሎት ሰጪ ማህበሩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና ያገለገለወን ተሽከርካሪ የሠሌዳ ቁጥር እንዲሁም ቀረጥና ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጠወን ማስረጃ ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ለገንዘብ ሚኒስቴር ይልካል፣

ለ) ጥያቄው የቀረበው በአዲስ የተሽከርካሪ አገልግሎት ሰጪ ማህበራት እና/ወይም አዲስ ተሽከርካሪ ለመግዛት ከሆነ የታክሲ አገልግሎት ሰጪ ማህበሩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ማስረጃዎችን ለገንዘብ ሚኒስቴር ይልካል፣

3/ የገንዘብ ሚኒስቴር የመብቱ ተጠቃሚ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ የሚገዛው ሙሉ በሙሉ በተበታተነ እና/ወይም በከፊል በተበታተነ የተሽከርካሪ አካል መሆኑን በማየት ለጉምሩክ ኮሚሽን ያስተላልፋል፡፡

4/ በሕግ ኃላፊነት የተሰጠው የመንግሥት መ/ቤት በሥራው የተለየ ባህሪ ምክንያት ለታክሲ አገልግሎት የሚውል የተለየ ተሽከርካሪ ግዥ ሚፈፀም የሚያስገድድ ሁኔታ አለ ብሎ ሲያምን ለፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፣ የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን የቀረበወን ጥያቄ የሚደግፍ ከሆነ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

## 11. <u>መብትን ስለማስተላለፍ</u>

በዚህ መመሪያ መሠረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው የተሸጡ ተሽከርካሪዎች ለሌላ ወገን ሊተላለፉ የሚችሉት በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

## 12. <u>የመብቱን አፈፃፀም ስለመገምገም</u>

1/ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን በጋራ በመሆን በየሦስት ወሩ የዚህን መመሪያ አፈፃፀም ይገመግማሉ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለሚካሄደው ግምገማ መነሻ እንዲሆን በፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለወን በማመጣጠን እና የአገር ወስጥ ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ ረገድ የተገኘወን ወጤት በሚመለከት በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የታክሲ አገልግሎትን በማሻሻል ረገድ የተገኘወን ወጤት በሚመለከት በትራንስፖርት ሚኒስቴር በየሦስት ወሩ ከሚደረገው ግምገማ አስቀድሞ ለገንዘብ ሚኒስቴር ይቀርባል፡፡

## 13. <u>የማሻገሪያ ድንጋጌ</u>

ለታክሲ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ስለሚገቡበት ሁኔታ ቀደም ሲል በተላለፉ መመሪያዎች መሠረት ሂደታቸው የተጀመረ ጉዳዮች በሥራ ላይ በነበሩት መመሪያዎች መሠረት አፈፃፀማቸው ይቀጥላል፡፡

## 14. የተሻሩ መመሪያዎች

ለታክሲ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ስለሚገቡ ተሽከርካሪዎች ቀደም ሲል የተላለፉ መመሪያዎች ተሽረው በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

## 15. መመሪያወየሚፀናበትቀን

ይህመመሪያከሚያዚያ 27 ቀን 2013 ዓ.ም.ጀምሮየፀናይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ቀን 2013 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*